# የልማት ዕቅዱ ፍሬያማነትና የጨለምተኞቹ ሃፍረት

ቶሎሳ ኡርጌሳ

Utolosa@yahoo.com

“ወርልድ ክራንች” (World crunch) መረጃዎችን ከዓለም አቀፍ ሚዲያዎች እየተነተነና እየተረጎመ በድረ ገፁ አማካኝነት የሚያሰራጭ እንዲሁም በዓለም ላይ የሚገኙ ጋዜጠኞችና ተርጓሚዎች የሚሳተፉበት ዕውቅ፣ ዝነኛና ተፅዕኖ ፈጣሪ የዜና አውታር ነው፡፡ መቀመጫውን ፓሪስ ያደረገው ይህ ግዙፍ ተቋም፤ በመረጃ ቋቱ ሰሞኑን አንድ ኢትዮጵያን የተመለከተ ዘገባ ሰድሯል— ኢትዮጵያ የመልካም ቁም ነገሮች ምንጭና የአፍሪካ ሞዴል እየሆነች የመጣች ሀገር መሆኗን በማተት፡፡

የሀገራችንን ፈርጀ ብዙ የልማት ጉዞዎች ለመገምገም “በችግርና ረሃብ ተምሳሌትነቷና ግንባር ቀደሚ ሀገር፣ እውን የአፍሪካ ሞዴል መሆን ይቻላት ይሆን?!” በሚል ርዕስ ጥናት ያደረገው ድረ- ገፁ፤ ለጥናቱ አዎንታዊ ምላሽ ማግኘቱን በስፋት አትቷል፡፡ አሃዞችን በማስደገፍ። እ.ኤ.አ. ከ1984 እስከ 1985 ዓ.ም በአስከፊ ረሃብና ድርቅ ትታወቅ እንደነበር የትላንት የነተበ ማንነታችንን በማስታወስ ጥናቱን ወደ መረጃ ቋቱ የሰደረው “ወርልድ ክራንች”፤ ኢትዮጵያ በተከታታይ ዓመታት ባስመዘገበችው እስከ አስር በመቶ የሚደርስ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማስመዝገብ በአፍሪካ የመሪነቱን ዘወድ እንደደፋች በአደባባይ ተናግሯል — ማንም ቢሆን በገሃድ የሚታየውንና የሚዳሰሰውን ሃቅ መካድ አይቻለውምና፡፡

ፍሎረንስ ቢጊ የድረ ገፅ ዘጋቢ ነው፡፡ የወቅቱን የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ በአንክሮ በመመርመር በካከለኛ ገቢ ካላቸው የምዕራቡ ሀገራት ጋር እያመሳከረ የሀገራችንን የልማት ጉዞ በታማኝና ሳይንሳዊ ትንታኔዎችብ ባዘለ ሁኔታ ያስረዳው ዘጋቢው፤ በኢትዮጵያ የተፈጠረው መካከለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ የገቢ ልዩነትና ማህበራዊ መስተጋብሩ እንደ ምዕራብ አውሮፓ አቻው የማይዋዝቅና ዋስትናው የተረጋገጠ መሆኑን ገልጿል፡፡ ጠማሪው የስኬቱን ምንጭም አልሸሸገም። ተስፋ ሰጪውና በአፍሪካ ተምሳሌቱ የተጠቀሰው የሀገራችን እመርታ ከምንም የተገኘ ሳይሆን፣ በሀገሪቱ ከተፈጠረው ባለ መካከለኛ ገቢ ማህብረሰብ የመገንባት ታላቅ ራዕይና ያላሰለሰ ጥረት እንዲሁም ድህነትን ለመዋጋት ህዝቡ ካለው ቀናዒ ቁርጠኝነት መሆኑን እማኝነቱን ሰጥቷል፡፡

ፍሎረንስ ቢጊ ለአብነት ያህል አዲስ አበባን ጠቅሷል፡፡ መዲናችን ከዓመታት በፊት ከምትታወቅበት ጥሩ ያልሆነ ገፅታ ፍፁም እየተቀየረች መምጣቷንና በመጠንና መልክ ብዙ ለውጦች ውስጥ መሆኗን አስረድቷል፡፡ ታዲያ የሀገራችንን ፈርጀ ብዙ ልማት ለመዘገብ ብዕሩን ያነሳው "የወርልድ ክራንች" ዘጋቢው ብቻ አይደለም፡፡ የቢ.ጂ.አይ (BGI) ጄኔራል ዳይሬክተሩ በርናርድ ኩሌይስም የነገ ማንነታችን ፍንትው ብሎ ተገልጦላቸዋል፡፡ የኢትዮጵያን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ አድናቂ የሆኑት እኚህ ግለሰብ፣ ከንዋኔው ከኬንያና ከአንጎላ ጋር ሲነጻጸር በሰማይና በምድር የሚወከል የንግድ ስልጠት መኖሩንም ጠቁመዋል።

የዓለማችን እጅግ ተነባቢና ግዙፉ ድረ- ገፅ "ዘ ታይም" (The time) በበኩሉ የኢትዮጵያን ልማት ላላመዘገብ አቅም አጥቷል፡፡ እናም በሰሞነኛ የመረጃ ቋቱ ሀገራችንን በተመለከተ ሰናይ ዘገባዎችን ወይም ሃቆችን አስፍሯል– ሀገራችን የነደፈችውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP) ስኬታማነትን በመገምገም፡፡ ሆኖም ገምግሞ መረጃውን ለቅርጫቱ ማሞቂያ አላዋለውም፡፡ ይልቁንም ሀገራችን ትታወቅበት የነበረውን የትላንት መጥፎ ገጽታ በመለወጥ ታላቅ እመርታ እያስመዘገበች መሆኑን ነው ያስነበበው፡፡ በሌላ አባባል አንዳንድ ጨለምተኛ ሞጋቾች ውድድሩ ሳይጀመር አሸናፊውን ባወቁበት ችኩል ድምዳሜያቸው ያጣጣሉትን ታላቁን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ኢ-ሳይንሳዊ ሚርትን ፉርሽ አድርጎታል– የማይቻል የሚመስለውን ነገር መቻላችንን በመመስከር፡፡ ድረ- ገፁ የዕቅዱን ስኬታማነት የመሰከረው ተጨባጭ ዋቢዎችን በመምዘዝ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በጤናው መስክ ከተነደፈው የአምስት ዓመቱ የልማት ግቦች አንዱ የሆነው የህጻናት ሞት በ40 በመቶ መቀነሱን ጠቁሟል፡፡ የዓለም ባንክ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ባለሙያ የሆኑት ላርስ ሞላርም ሙያዊ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መንግስት ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ ለመተግበር ቁርጠኛ መሆኑ እንደሚያስደንቅ የተናገሩት ጠበብቱ፣ ሀገራችን ባለ ተስፋ መሆኗንም አስረድተዋል፡፡

እርግጥ ሀገራችን በዕድገት ጎዳና ላይ እንደምትገኝ ታላላቅ የመገናኛ ብዙሃንም ይሁኑ የምጣኔ ሀብት ጠበብቶች ሲዘግቡና ሲመሰክሩ የሰሞኑ የመጀመሪያቸው አይደለም፡፡ ብዙዎች ብዙ ብለውለታል፡፡ ስለ ፈርጀ ብዙው የልማት እምርታችን መገናኛ ብዙሃንም ይሁኑ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሀገራችን እየተለወጠችና እያደገች መሆኗን የሚመሰክሩ ስራ ስሌለላቸው ወይም እኛን ለመደለል አይደለም፡፡ አዎ! የሚነግሩን የምናየውንና የምንዳስሰውን ጉዳይ ነው፡፡ የዜና ሽፋናቸውንና ጊዜያቸውን አጣበው ስለ እኛ መዘገባቸው፣ መፃፋቸውና ከሙያቸው እየተነሱ መመስከራቸው አንድም ባለ ተስፋዎች መሆናችንን ስላወቁ አሊያም እውነትን መመስከርና ለዓለም ማሳወቅ ስራቸው በመሆኑ ነው፡፡ ሁኔታውን በሌላ መልኩ ስንመለተው ደግሞ ለወዳጆቻችን ዜና ብስራት መሆኑ አይቀርም።

ዳሩ ግን በአንድ እውነት መግባባት ያለብን ይመስለኛል፡፡ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎችና የምጣኔ ሀብት ጠበብቶች የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታችንን ፍሬያማነት መመስከራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋነኛ ባለጉዳዮች እኛው ነንና፣ የእኛ ምስክርነት ከማንም የበለጠ ታማኝ ይመስለኛል– ነገሩ "ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ" እንዲሉት ነውና። የልማቱ አካልም፣ ተዋናይም፣ ተጠቃሚም እኛው በመሆናችን ከሶስተኛ ወገን ይልቅ የእኛ ቃል የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ቢተነትን ይደመጣል፤ ትርጉም አለው፡፡ እርግጥ እነሱም ቢሆኑ ሃቁን ቦርብረው እንጂ በትርጁማን ተነግሯቸው አልመሰከሩም፡፡

እንግዲህ ይህን በፍሬያማነቱ መንግስት ተማምኖ የነደፈውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነበር– አንዳንድ አዋቂ ነን ባይ የመድረክ ተጣማሪዎችና የዲያስፖራ ጨለምተኞች ገና ጉዞው ሳይጀመር ትክት ብሏቸው "ህልም ነው" በማለት ዕቅዱን ለማብጠልጠል ቀድመው የዘመቱት፡፡ እነዚህ ጨለምተኛ ግለሰቦች ማውራት እንጂ መስራት ስለማይችሉ አንድ እርምጃ እንኳን ሳይራመዱ ሃሞታቸው ቢፈስ አይገርምም፡፡ የሰው ልጅ ነገሮችን የሚመዝነው በህሊናው ጥበትና የአቅሙን ያህል በመሆኑ የዕቅዱን ስኬታማነት ሰማይ የማከክን ያህል ማክበዳቸው አይገርምም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን 'ከአቅም በላይ የታቀደ፣ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል የቀረበ… ቅብጥርሴ' በማለት ዕቅዱን ለማጣጣል የተጣደፉት ጨለምተኞች ሁሉ ዛሬ በውጤታማነቱ እያፈሩ ነው፡፡ መቼም ከጥናት የበለጠ ምክንያታዊ ማስረጃ የለምና የዕቅዱን በተግባር መተርጎም የሚቃወሙ ሟርተኞች ባይጠፉም፤ ስለ ስኬታማነቱ የሚሟገቱ የሚኖሩ ግን አይመስለኝም– "የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ወይም በአንድ ራስ ሁለት ምላስ" እንዳይባሉ ካልሰጉ በስተቀር። አዎ! የዕቅዱ ፍሬያማነት ከወዲሁ እየተመዘገበና እየተመሰከረ ነው፡፡

ለነገሩ ዕቅዱ ለስኬት እየበቃ ያለው ቀላል ስለሆነ አይደለም፡፡ ይልቁንም ግዙፍና መልከ ብዙ ፕሮጀክቶችን ያቀፈ ነው፡፡ ዳሩ ግን የዕቅዱ አካላት የቱንም ያህል የገዘፉና የማይሞከሩ ቢመስሉም፤ መንግስት ወትሮም ወደ ስራ የተገባው የህዝቡን ይሁንታ አግኝቶና በጥናት ተደግፎ ስለነበር ስኬታማነቱ የሚያጠራጥር አልነበርም፡፡ ህዝብ ያመነበት ልማት የህዝብ ነውና ስለ ህዝብ ስኬታማነት ማመንታት ህዝብን መናቅ እንዲሁም እውነትን መካድ ይመስልኛል፡፡ መንግስት ስለ ዕቅዱ ስኬታማነት እርግጠኛ ሆኖ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ወደ ትግበራ በገባበት ወቅት፣ በዋነኛነት የተማመነው በህዝቡ ነበር፡፡ እርግጥም ህዝቡ ዋነኛ የልማት ዋስትና መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ቀደም ሲል በተከታታይ የተመዘገቡ ፈጣንና ፈርጀ ብዙ እመርታዎችም ከፍ ያለና የላቀ ዕድገት ማስመዝገብ የሚቻል መሆኑን የሚጠቁሙ ነበሩ፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍና ከድህነት ተምሳሌትነት ለማውጣት የምንችለው ጠንክረንና በትልቁ አቅደን

በመስራት እንጂ ገና ለገና የተለጠጠ ዕቅድን በመፍራት አይደለም፡፡ ህዝቡም ሆነ መንግስት በአንድ ቋንቋ እንደሚሉት፤ ልክ እንደ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ወገብ የሚያጎብጡ፣ ነገር ግን በሃፍረት የተደፋ አንገታችንን ቀና ማድረግ የሚችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መቀመር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው—የሞት ሽረት ትንቅንቅ። ያ ካልሆነ የምንፈልጋት ገናና ኢትዮጵያ፣ ህዝቦቿ ከድህነት አረንቋ የወጡባት ሀገር አትመጣም – አለመምጣት ብቻም ሳይሆን እንደ ሀገርና ህዝብ የመኖር ህልውናችን መስቀለኛ መንገድ ላይ መሰንቀሩም የሚቀር አይመስለኝም፡፡

እናም ትልቅ ማቀዳችን የትልቀነታችን ወይም ትልቅነታችን ለመቀዳጀት መቆጨታችንን የሚያመላክት እንጂ፤ እንዲሁ በገፈናው ጨለምተኞች በቅብብሎሽ አጀንዳቸው እንደሚያወሩት አልነበረም፡፡ ለምን ቢሉ ለመልካምነት፣ ለመለወጥና ከድህነት ለመላቀቅ እንኳንስ በትልቁ አቅዶ መንቀሳቀስ ቀርቶ በትልቁ ማሰብ በራሱ ሰናይ ነገር ነውና። እናም አንዳንድ “የጨለማው ዘማሪዎች” በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የዕቅዱን ግዙፍነት ምክንያት ባልሆነ ምክንያታዊነት እየተንተራሱ ያሻቸውን ቢሉም፤ ዕቅዱ ዛሬ ላይ እየተቻለ መሆኑን ከእኛ አልፎ ባዕዳን እየመሰከሩለት ነው፡፡

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ሀገራችን በእስካሁን ጉዞዋ ያስመዘገበቻቸው የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባህል ግንባታ ትሩፋቶች ለህዝቧ ብርታት ሆነዋል፤ ሆነውናል። ትላንት ከዛሬው የላቀ መስራት እንደምችል ትምህርት ሰጥቶናል፡፡ እናም ምንም እንኳን በትላንት አጥጋቢ ድሎቻችን እየተመጻደቅን ዛሬን በማባከን ነገን ከመስራት የምንቦዝን ባንሆንም፣ ባለ ተስፋ መሆናችንን ግን ቢያንስ በእጃችን በገቡ የልማት ድሎች ልበ ሙሉዎች ብንሆን ተገቢ ነው— ብልህነት ነውና። ብልህነት በትልቁ አቅዶ በትልቁ መስራት እንጂ በትንሹ አቅዶ በትንሹ መስራት አይደለም፤ የትም አያደርስምና፡፡ ለነገሩስ “ትልቅ ተመኝ፣ ትልቅ እንድታገኝ” ይባል የለ?– እርግጥም ትልቅ ተመኝተን ትልቅ እያገኘን ነው፤ የታላቆች ታላቅም ልንሆን ነው፡፡

ምንም እንኳን የዕቅዱ ስኬት የጨለምተኞችንና የነገ ታላቅነታችንን ፈሪዎች ያህል እንደሚደሰኩሩት እግሮች ያሉበት ባይሆንም፤ ታላቁ የልማት ዕቅድ አልጋ በአልጋ እንደማይሆን ግን ማንም ይስተዋል ብዬ አላስብም፡፡ በዓለማችን ላይ እንደ ቦይ የሚፈስና ተግዳሮቶች የማያጋጥሙት ዕቅድ የለምና። ድል በትግል እንጂ በዕድል የማይገኝ መሆኑም እንዲሁ፡፡ መንግስትም ሆነ ህዝቡ በተደጋጋሚ እንደሚሉት ውጣ ውረዶችና ተግዳሮቶች መኖራቸው አይጠረጠርም፡፡ ግና መንግስት ታሳቢ ችግሮችን አስቀድሞ በመቀመር መሳ ለመሳም ታሳቢ መፍትሄዎችንም አዘጋጅቷል፡፡ ለአብነት ያህል የማስፈጸም አቅም ውስንነት በዕቅዱ ስኬታማነት ላይ የራሱን አሉታዊ ድርሻ ሊያሳርፍ እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርምና ዕቅዱን መተግበር ግድ ነበር፡፡ እናም መፍትሔው የማስፈጸም

አቅም ችግሮችን ለመቅረፍ ፈፃሚዎችን በማብቃትና በማረም የታቀዱ ፕሮጀክቶችን መተግበር እንጂ፣ ማፈግፈግ አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ መንግስትና ህዝብ ያደረጉትም ይህንኑ ነው፡፡

እናም ዕቅዱ ይፋ ከሆነበት ከ2003 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ መንግስትና ህዝቡ መደማመጥና ይበልጥ መግባባት በመቻላቸው ብሎም በዕቅዱ መሰረት የተያዙ ትልሞችን በጊዜ ገደባቸው ውስጥ በማከናወናቸው፣ ታላላቅ መገናኛ ብዙሃንና የዓለም አቀፉ ማህብረሰብ እንዲሁም የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ደረታቸውን ነፍተው ሊመሰክሩ ችለዋል። እኛም ከወዲሁ ነገ የተሻለች ሀገር እንደምትኖረን መተንበይ የቻልንበትን ድል እያስመዘገብን መሆናችንን እነሆ እንናገራለን፡፡ አዎ! ህዝቡ በዕቅዱ ስኬታማነት በመተማመኑ፣ የልማቱ ባለቤት በመሆኑና የመንግስት ቁርጠኝነት የማያወላውል ስለሆነ የማይሞከር መሳዩን ግዙፍ ዕቅድ ያለምንም መሸራረፍ እልባት ላይ ለማድረስ ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ዕቅዶቹ ሙሉ በሙሉ ተሳክተዋል እያልኩ እንዳልሆነ ሊታወቅልኝ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የዕቅዱ ዘመናት ሊጠናቀቁ ገና ሁለት ዓመታት ወደፊት የሚቀሩ በመሆናቸው ነው። በቀሪዎቹ ጊዜያት ቀሪ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ከፍጻሜ እንደሚደርሱ ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ እስካሁን የተከናወኑት ታላላቅ ስራዎችን እንደ ሞራል በመውሰድ በቀሪዎቹ ሁለት ዓመታት በርካታ ፍሬያማ ተግባራትን መከናወናቸው አይቀሬ ነው— ምንም እንኳን አንዳንድ ጨለምተኛና የጥላቻ ፖለቲካ ህሊናቸውን የጋረደባቸው ግለሰቦች ሃቁን በመደፍጠጥ እነዚህን ምስክርነቶች ብሎም እየተመዘገቡ ያሉ የጨባጭ ስኬቶችን እያዩ ያለ ሃፍረት የሌላ ሀገር ዜጋ ተመስለው የዕቅዱን አለመሳካት ሊነግሩን ቢሞክሩም፡፡

ዛሬ ግን በአሉባልታና በውሸት የሚነዳ ትውልድ የለም— አመዛዛኝ እንጂ። ውጤታማነቱን ዓለም እየመሰከረ ያለውን የታላቁን የልማት ዕቅድ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው እንደማይሳካ የሚያወሩ ጨለምተኞች ፉርሽ እየሆኑ ነው። እናም በሁለቱ ቀሪ የአምስት ዓመቱ ዕቅድ ዓመታት እነዚህን አደናቃሪዎች የምንሰማበት ጆሮ የለንም። ስለሆነም በአንድ በኩል ዕቅዱ ከፍጻሜው የሚደርስበትን ዕድል በመፍጠር የልማት ንቅናቄው አካል በመሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የከንቱ አሉባልተኞችን ጉንጭ አልፋ ክርክር በመመከት ለጋራ ቤታችን ልዕልና መትጋት ይጠበቅብናል፡፡ በሃሳብም፣ በሞራልም ፣በጉልበትም ሆነ በዕውቀት የከርሞዋን ሀገራችንን ዛሬ መስራት አለብን፡፡

እንደሚታወቀው ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር አቅዳና ከህዝቧ ጋር መክራ ሌት ተቀን እየሰራች ነው፡፡ እንግዲህ ይህን የኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ሥርዓት የማሳለጥና ለቀጣይ ልማታችን ምቹ መደላድል ለመፍጠር ነው— ኢትዮጵያ ግዙፍና የማይሞከሩ ፕሮጀክቶችን ነድፋ በተግባር መንቀሳቀስ የጀመረችው፣ ውጤት ማስመዝገብም የቻለችው፡፡ ከዓመታት በኋላ በኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚተካውን የግብርናውን ዘርፍ በ15 በመቶ ለማሳደግ ዕቅድ ተይዟል፡፡ ታዲያ ይህን ያህል ወገብ የሚያጎብጥ ዕቅድን ለማሳካት

እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር መንግስትና ህዝብ መክረው ወደ ተግባር ሲገቡ፤ አንድም ቀደም ያሉ ተከታታይና ፈጣን ዕድገት በመቀመር አሊያም የአፈጻጸም ችግሮችን በመቅረፍ የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓቱን ይበልጥ ለማዘመን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ዛሬ ዘመናዊ የግብርና ማዕከላት ተስፋፍተዋል፤ እየተስፋፉም ነው፡፡ ትላልቅ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተገንብተዋል፤ በመገንባት ላይም ይገኛሉ።

ሁላችንም እንደምንገነዘበው ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የመሰረተ- ልማት መስክ በደም ስርነት ይመሰላል፡፡ ይህን የልማት ዋነኛ ዘርፍ ለማዘመን ዘመናዊ መንገዶች እየተገነቡ ነው፡፡ ተገንብተዋልም፡፡ በተለይም ከግብርናው ምርት እመርታ ጋር ምርታማነቱ አብሮ የሚያሻቅበውን ሸቀጥ ለማጓጓዝ የባቡር ትራንስፖርት ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ዘመናዊ የባቡር መስመር ዝርጋታው ተጀምሯል፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም የተዘነጋ አይደለም፡፡ በታዳሽ ምንጮች በተለይም በግድቦች ግንባታ ከ6 ሺህ እስከ 8 ሺህ ሜጋ ዋት ድረስ በማመንጨት በድምሩ እስከ 10 ሺህ ሜጋ ዋት የመብራት ኃይል የማመንጨት ስራው ተጧጡፏል። እዚህ ላይ ሌት ተቀን እየተሰራ ያለውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ በአብነት ያስታውሷል!፡፡ በምድረ አፍሪካ በቴሌኮሙኒኬሽን ዝማኔ ግንባር ቀደም ከሚባሉት ግብጽና ደቡብ አፍሪካ ጋር የሚወዳደር የመረጃ መረብ (Internet) እንዲኖረንና ከ40 ሚሊዮን (የአሁኑን ህዝብ ቁጥር ግማሽ ያህል) የሞባይል ተንቀሳቃሽ ስልክ ተገልጋይ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ስራውም ውጤት እያስገኘ ነው።

በትምህርቱ ዘርፍ በኩልም ቢሆን ከታቀደው በበለጠ ስኬቶችን ለማስመዘገብ ተችሏል፡፡ በአንደኛና ሁለተኛ እንዲሁም በመሰናዶ ብሎም በቴክኒክና ሙያ ዘርፎች አጥጋቢ ውጤቶች እየተገኙ ነው። ጥራቱን የጠበቀ የመደበኛና ዘመናዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአራቱም የሀገራችን አቅጣጫዎች እየተስፋፉ ነው፡፡ እርግጥ ጊዜና ቦታ ስለሚገድቡኝ እንጂ ሌሎቹንም የዕቅዱን ስኬቶች በሙሉ መዘርዘር ይቻል ነበር። ይሁንና እነዚህ የየዘርፉ ክንዋኔዎች ጉልህ ማሳያዎች በመሆናቸው የሌሎቹን ወጤቶችን በእነዚሁ የልማት እመርታዎች መነፅር ውስጥ ማየት ይቻላል።

ያም ሆነ ይህ ግን እነዚህ ስኬቶች መንግስት የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዕውን በማድረግ ዜጎችን የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ እንዲሁም ሀገራችንን ከድህነት ለማላቀቅ መሻቱ እርግጥም ከምንም ተነስቶ እንዳልነበር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ባቀዳቸው የተጠኑና የተቀመሩ ስልቶች ውስጥ ህዝቡ የሚኖረውን የማይተካ ሚና ተማምኖ እንዲሁም ካለፈው የዕድገት ውጤታማነት ተሞክሮው የልማት ትልሙ ገቢራዊ እንደሚሆን ስላወቀ ነው፡፡ ይህም አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ዕቅዱ ምንም እንኳን የተለጠጠ

ቢሆንም፤ የሚቻል እንደሆነ ግን መንግስትና ህዝቡ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተምሳሌት ሆነው ማሳየታቸውን ያረጋግጣል –ሁላችንም እንደምናስተውለውና ባዕዳንም እንደመሰከሩት፡፡

ታዲያ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በዚህ ተምሳሌታዊ ጉዞ ችግሮች አልነበሩም ማለት አይደለም። በአንዳንድ የአሰራር እንከኖች ድሮም ዘንድሮም መኖራቸው አይቀርም፡፡ የሰው ልጅ መላዕክ አይደለምና ተግዳሮቶች አብረውት ይኖራሉ፡፡ እናም መታሰብ ያለበት ችግሮችን ስለ መቀነስ እንጂ ፈፅሞ ስለ ማጥፋት አይደለም፡፡ በመሆኑም መንግስትና ህዝቡ ከዕቅዱ አኳያ ያሉትን ችግሮች መቀነስ ችለዋል፡፡ ችግሮችን መቀነስ በመቻላቸውና አሰራሮችን በማዘመናቸውም ነው– ዓለም እየመሰከረው ያለውን ዕድገት እያስመዘገቡ ያሉት፡፡ እርግጥም የባህር ማዶ ሰዎች በጥናታቸው እንደመሰከሩት እንዲሁም ድፍን ኢትዮጵያዊያንን ያማለሉ፣ ተስፋ የሰጡና ነገ የተሻለች ሀገር እንደምትኖረን ብርሃንን ያመላከቱ ድሎችን ማስመዝገብ ጀምረናል፡፡ እናም ስለ ጨለምተኞችና አውርቶ አደሮች መጨነቅ የለብንም፡፡ ዕቅዱ የማይሳካ መሆኑን በማብጠልጠል ወሬ የተጠመዱ ፀረ - ልማት ኃይሎችን ወደ ኋላ ትተን፤ በቀሪዎቹ የዕቅዱ ዓመታት ወደ ነገው ተስፋችን የምንወጣበትን ማማ አጥብቀን በመያዝ ይበልጥ ወደ ተሻለ ከፍታ ላይ መረማመድ ይኖርብናል፡፡

እናም እያንዳንዳችን የሚጠበቅብንን ከተወጣን፣ እንደ ትናንቱ ነገም አለመቻልን አስወግደን መቻልን ከቻልን፣ በአንድነታችን ባለው ልዩነታችን ይበልጥ ከፀናንና በህብረ- ብሔራዊነታችን ይበልጥ ተጠናክረን ከቀጠልን ከወዲሁ እየተመሰከረለት ላለው ብሩሁ "የነገ ሰውነታችን" መድረሳችን አይቀሬ ነው፡፡ እነ ቻይና፣ ህንድና ኮሪያ ትልቅ አቅደው ትልቅነትን ያገኙት ስለተመኙ ብቻ አይደለም– ሌት ተቀን ስለተጉ የሚጠብቁትን ድል ተጎናፀፉ እንጂ፡፡ ታዲያ እኛም ትጋታችንን እንትጋ፡፡ ቀበቶአችንን ይበልጥ ጠበቅ አድርገን እነ "ወርልድ ክራንች"፣ "ዘ ታይም"፣ እና "ዘ ኢኮኖሚክስ" ከፍ ሲልም የዓለም ማህበረሰብ ያለማቅማማት እያወደሰው ያለውን ፈርጀ ብዙ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታችንን በርትተን ማስቀጠል ይጠበቅብናል–"የነብርን ጭራ አይዙም፣ ከያዙም አይለቁም" እንዲሉ አበው፡፡ አበቃሁ!